# ከትርጉም አክሮባት እና ከቅጽል ባሻገር ኤች አር ሲመነዘር
## (ኤች አር ለምን? ኤች አር ለማን? ኤች አር የማን?)
## ክፍል ሁለት

ከዘሪሁን ተሾመ

**ኤች አር ከሰሞኑ (... እንደ ንጉሡ ... እና እንደ ሙቀጫው ወይስ ...?)**

የክፍል አንድ ፅሑፌን ካቀረብኩ ወዲህ ባሉት ሃያ ቀናት በኤች አር 2003 ረቂቅ አዋጅ ዙሪያ የታዩ ክንውኖች አሉ። ሰነዱ ከፅንሰት እስከ ውልደት ከበቃበት 20 ወራት የፈጀ እድሜ ርዝመት አንፃር እጅግ አጭር በሆነው በዚህ ጊዜ ያስተዋልናቸው የእነዚህ ክንውኖች ይዘት እጅግ ገላጭነት ያለው፤ ዋነኛ የሆኑ ተዋናዮችም ያሳተፈ ነው። ውልደቱ በአሜሪካ ፓርላማ የተበሰረውን ሰነድ የፊታችን ጥር ክርስትና በማንሳት ህግ ሆኖ እንዲተገበር ማፅደቅ የሚጠበቅበት ሴኔት (የፓርላማው የላይኛው ምክር ቤት)፤ ይህን ተከትሎም የማስፈፀም ኃላፊነት የሚኖረው የአሜሪካ መንግስት፤ ኢላማ ተደርጎ ህጉ ተፈፃሚ የሚደረግበት የኢትዮጵያ መንግስት፤ ረቂቁ ለዚህ እንዲበቃ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውንና ክብራቸውን ሰውተው በአዝማችነት የተሰለፉ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች እንዲሁም በአሜሪካ ፖለቲካ አንፃራዊ ተፅዕኖ ያለው የአሜሪካ ሚዲያ በዚህ ረገድ የተሳተፉ ዋነኛ ተዋናዮች ሆነው እናገኛለን። ለመጥቀስ ያህል በቅርቡ አዲስ አበባን የጎበኙት ሴናተር ኢንሆፍ እና ጓዶቻቸው፤ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና ባለስልጣኖቻቸው፤ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች የሆኑት አቶ ልደቱ፣ ዶ/ር በየነ፣ ዶ/ር መረራ፣ አቶ ተመስገን፣ ወዘተ. ከሀገር ውስጥ፤ አቶ መስፍን መኮንን፣ ሰለሞን በቀለ፣ ስዩም ሰለሞን፣ ወዘተ. ከሀገር ውጪ፤ እንዲሁም የፖል ቶክ ፎረሞች እና እውቁ የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ይገኙበታል።

በኤች አር ዙሪያ በተከታታይ አስተያየቶቻቸውን አጋርተው አቋማቸውን አሳውቀውናል። የሰነዱ ይዘት እና ያለፈበት ሂደት ይበልጥ ተብራርቶልናል። በዚህ አጋጣሚም የሆነውንና ያልሆነውን፣ ያዘለውን ተቃርኖና ተጣጣሚ መልእክት፣ በጅምላ ተሸፍነው የነበሩ አቋሞችን ምንነት በተሻለ መገንዘብ ችለናል። በአጭሩ ኤች አር ለምን? ለማን እና የማን እንደሆነ ተገላልጧል። መፃዒ እጣ ፈንታው ምን ሊሆን እንደሚችልም መሰረት ያለው ግምት መስጠት ከሃያ ቀን በፊት እንደነበረው የከበደና የራቀ ከመሆን ወርዷል።

ይልቁንም ከዋነኛ አርቃቂዎቹና የድጋፍ አዝማቾቹ አንፃር «ባይታየውም ይታያል፣ ባይለብሰውም ለብሼዋለሁ ብሎ ያመነውን የሌለ ድንቅዬ ልብስ መርጦ እርቃኑን የቆመውን ንጉሥ» ታሪክ እየመሰለ መጥቷል። እንደ ሂደት ሲታይ ደግሞ የረቂቁ ነገር *«ወጣ ወጣ እና እንደ ሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ»* ለሚለው የቀረበ ይመስላል። ስለሆነም በዚህ የፅሑፌ ክፍል **ኤች አር 2003 ለምን እንደ ሸንበቆ ተመዝዞ እንደ ሙቀጫ መንከባለል እንደጀመረ፣ ዋነኛ ተዋናዮቹም እንደ ጠቀስነው ንጉሥ እርቃናቸውን ወደ መቅረት እንደተጠጉ ለመጠቆም** እሞክራለሁ።

**የኤች አር ጉራጅ/ሙት መነሻዎች እና ተቃርኖዎች**

በተክሌ አታላይ ተርጓሚነት «ጥምረት ለኤች አር 2003» (ኮአሊሽን ፎር ኤች አር 2003 ወይም 5680) የሚባል ስብስብ ለአንባቢዎቹ ያቀረበው የረቂቁ ሰነድ «የመጠቀ የአማርኛ ትርጓሜ» (ኤክስትራ ኦርዲነሪ ትራንስሌሽን) ክፍል ሶስት ውስጥ «ግንዛቤዎች» በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ከገፅ 2 እስከ 4 የተቀመጡ 20 ዝርዝር ነጥቦች የሰነዱ አርቃቂዎች መነሻ ያደረጉትን የኢትዮጵያ እውነታና ሁኔታ ንባብ ወይም ግንዛቤ አመልካች ነው። በዚህ ፅሐፊ እምነት እነዚህ የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ አጠቃላይ ሂደትም ሆነ ወቅታዊ ጥሬ ሃቆች በተመለከተ በኤች አር 2003 ረቂቅ መነሻ ተደርገው በደጋፊ ማስረጃነት የተጠቀሱ ጭብጦች በአመዛኙ ጉራጅ ወይም ሙት የሆኑ እውነቶች እና በእርስ በርስ ተቃርኖም የተሞሉ ናቸው። በሌላ አባባል የተጠቀሱት ጭብጦች በአንድ ወቅት የነበረ ወይም ያጋጠመ ሆኖም በሂደት የተቀየረ (ማለትም ሙት)፣

በዚህም ደረጃ ቢሆን ተመርጦ የተቀነጨበ ወይም ጉራጅ የአንድ ወቅት እውነታ የሚያመለክቱ ናቸው:: አንዳንድ አስረጂዎችን ልጥቀስ::

በተራ ቁጥር 6 እና በተራ ቁጥር 9 እንደተጠቀሰው ከቀዳሚው ሁሉ የተለየ ሰፊ ተሳትፎና የጦፈ ፉክክር የታየበትን የግንቦት 1997ዓ.ም ምርጫ ተከትሎ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ለሞትና ለአካል ጉዳት፣ ንብረታቸውም ለውድመት ተዳርጓል:: በሺዎች የሚቆጠሩም ለእስር፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ደግሞ ፍርሃት ላጠላበት የአንድ ሰሞን ህይወት ተዳርገው ተንገላትተዋል:: ይህ አንደኛው ግማሽ እውነት ነው:: የዚያኑም ያህል ይህ እንዲፈጠር ምክንያት የሆነው ሁኔታ ሊከሰት የቻለው ደግሞ አርቃቂዎቹ እንዳመኑት (ሰላማዊ ነው የሚለው ውጤቱን የማይቀይር ማምለጫ ሳይዘነጋ)የተጠቀሱት የተቃዋሚ አመራሮች አክራሪ ክንፍ ምርጫውን አሸንፈናል ብለውም ይሁን ተጭበርብሯል ከሚል «ጥርጣሬ» በመነሳት ካደረጉት ጥሪና ቅስቀሳ በመነጨ ነው:: ከጥርጣሬ ባለፈ ተገቢ መሰረት በሌለው እምነት ለዚህ መሰል ህልፈት ዜጎችን ሊዳርግ ወደቻለ ሂደት የማምራቱ ትርፍና ኪሳራ ስሌት ስህተተኛነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አክራሪዎቹ የተቃዋሚ መሪዎች ይህን እርምጃ ከመውሰድ እንዲታቀቡ የሚያበረታታ አማራጭ መንገድና እርምጃ በወቅቱ ነበራቸው:: በተጠቀሰው የአማርኛ ረቂቅ ትርጓሜ ተራ ቁጥር 5 እንደተቀመጠው በምርጫው ተቃዋሚዎች «ከ12 ወደ 170 የፓርላማ መቀመጫ፤» የትኛውንም የሀገሪቱ ክፍል ካለማስተዳደር የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማዕከል የሆነችውን እና በሀገሪቱ ካሉ ሶስትና ከዚያ በላይ ክልሎች የተናጠል ህዝብ ብዛት የበለጠ ህዝብ ያላት አዲስ አበባ ለማስተዳደር የበቁበትን ውጤት አግኝተው ነበር:: የተፈጠረው ቀውስ መነሻም በወቅቱ ይህን ውጤት በገዢው ፓርቲ በመነጠቃቸው አልነበረም:: ከዚህ ያለፈ ውጤት አስመዝግበን ተጭበርብረናል የሚል እንጂ:: ይህ ደግሞ አርቃቂዎቹ በተራ ቁጥር 6 እና 7 እንዳመኑት የጋራ መድረክ በሚባለው አማካይነት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳታፊ በሆኑበት ምርጫ ቦርዱ በወቅቱ እያየው የነበረ ጉዳይ ነው:: ማስረጃዎችን አጠናቅረው አቤቱታቸውን በማቅረብ በጊዜው ማጣራት የተባለው ሂደት የተጀመረው፣ በዚህም ላይ ተመስርቶ በማጣራቱ አቤቱታው በተረጋገጠባቸው የተወሰኑ ጣቢያዎች ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ተደርጓል:: በመሆኑም የአርቃቂዎቹ መነሻና ማስረጃ ሆነው የተጠቀሱት እነዚህ ነጥቦች ይህንን የእውነታውን አንድ ክፍል ቆርጦ በመጣል ወይም በመጉረድ ላይ የተመሰረቱ ናቸው::

በተያያዥ በተራ ቁጥር 8 «...የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ በኢትዮጵያ የከፋ ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ ይህ ሁኔታም እስከ አሁን ምንም መሻሻል አላሳየም...» የሚለውም ሆነ በተመሳሳይ በተራ ቁጥር 9 *«... አሁንም የተቃዋሚ መሪዎች፣ ደጋፊዎችና የቤተሰብ አባላት በፀጥታ ኃይሎች መንገላታታቸው አላቆመም...»* በማለት የተጠቀሰው ነጥብ፤ በሰኔ 1997 እና በህዳር 1998ዓ.ም ያጋጠመን ክስተት፣ ረቂቁ በኮንግሬስ እስከፀደቁበት ድረስ ቋሚና የቀጠለ በማድረግ መነሳታቸውንም ያመለክታል:: በተመሳሳይ በተራ ቁጥር 7 እንዲሁም 10 አቶ ኃይሉን፣ ዶ/ር ብርሃኑን ወዘተ. አስመልክቶ የሚያነሱት የእስረኝነት እውነትም ሆነ *«...በሀገር ክህደትና የዘር ማጥፋት ወንጀል»* የተመሰረተባቸው ክስ በሚል የሚጠቅሱት ይህንኑ የነበረ ግን የተቀየረ ያልነውን እውነታ ቋሚ አድርጎ መመልከትን የመረጠ ነው:: ይሁንና በተራ ቁጥር 9 *«... ብዙዎች ግን ተፈትተዋል»* በማለት የጠቀሱት ተቃራኒ እውነት እንዲሁም በእነርሱም አስገዳጅ ግፊት ሆነ ግለሰቦቹ በጠየቁት ይቅርታና የወቅቱ መንግስት ፈቃደኛ ሆኖ በመቀበሉ የተነሳ ከእስር ተፈትተው ለረቂቁ ድጋፍ በመስጠት ከመፅደቁ በፊት ሊመሰክሩ የበቁበት እውነታ ይህንን የሚያፈርስ አስረጂ ነው:: ለዚህ ለመብቃትም በሰነዱ *«... ነፃነት የሌለው ወይም በመንግስት ነፃነቱን እንደተነጠቀ...» ደጋግመው የሚያነሱት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ቢያንስ ከመፈታታቸው ወራቶች አስቀድሞ «የሀገር ክህደትና የዘር ማጥፋት»* የሚለውን የክስ አንቀጽ ውድቅ አድርጎ ነፃ እንዳደረጋቸው አውቆ መዘንጋትን የመረጠ ነው::

እነዚህ የእውነታው አንድ አካል የሆኑ ጭብጦች ወደ ጎን ተደርገው ባለበት ሁኔታ የተጠቀሱትን የእስርና የክስ ግማሽ እውነቶች (ያውም የአንድ ወቅት) ብቻ ገዢ መስፈርት በማድረግ በተራ ቁጥር 10 *«... እነዚህ እርምጃዎች በሀገሪቱ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን በወንጀል ሰበብ ለማጨናገፍ...»* እንዲሁም *«...የነፃው ፕሬስ የሲቪል ማህበረሰቡን... ህልውና ለማጥፋት ...» የተቃጡ ናቸው ብሎ መደምደም እና የኢትዮጵያ መንግስት «...ለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ያለውን ቁርጠኝነት»* ከጥያቄ መክተት እጅግ የተለጠጠ ከመሆን ያለፈ የእውነታ ድጋፍ አይኖረውም:: የአሜሪካን ዴሞክራሲ (ያውም ከለጋው የኢትዮጵያ ጥረት እጅግ የራቀውን) በጓንታናሞ ቤይ እስረኞች መብት ረገጣ ወይም በሎስአንጀለሱ ሮድኒ ኪንግ ግጭት ወዘተ. ላይ ብቻ ተመስርቶ በመመዘን ድምዳሜ ከመስጠት እምብዛም የማይለይ ቁንፅልነት አመላካች ነው::

በተመሳሳይ መልኩ በተራ ቁጥር 12 እና 13 በተጠቀሰው መልኩ ተሰይሞ ይህንኑ የድህረ ምርጫ ችግር ያጣራው ኮሚሽን አስመልክቶ በተራ ቁጥር 16 አርቃቂዎቹ መነሻ ብለው ያስቀመጡትን *«... የአጣሪ ኮሚሽኑ ሊቀ መንበር እና አባላት ... በአስቸኳይ በመሰብሰብ ውሳኔያቸውን እንዲቀይሩ የጠ/ሚ/መለስ ዜናዊ ከፍተኛ አማካሪ ትዕዛዝ ሰጥተዋቸው ነበር»* በማለት መደምደም፤ አለፍ ሲልም ከዚህ አንድ ክስተት በላይ የሆነውን (የተባለው ማስፈራራት ተፈፅሟል የሚለውን ብንቀበል እንኳን) የኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ሂደት በአጠቃላይ በመመዘን የህልፈት ብይን ማሳለፍ ከመረጃም ሆነ ከእውቀት እጥረት የመነጨ ሊባል አይችልም:: ይልቁንም የኮሚሽኑን ሊቀ መንበርና አባላት ለተጠቀሰው ማስፈራሪያ ያጋለጣቸው *«የማጣራት ውጤት»* ማስረጃዎች ቢያንስ በፀጥታ ኃይሎች እንዲወረስ መንግስት ሳያደርግ ኃላፊዎቹ ከነመረጃቸው ከሀገር በመውጣት በህዳር 1999ዓ.ም ለአሜሪካ ኮንግሬስ ምስክርነት መስጠታቸው ያዘለው ተቃርኖ ግዙፍ ነው:: ቢያንስ የተጠቀሰው ማስፈራሪያ መንግስታዊ ወይም ስርዓታዊ ሳይሆን ግለሰባዊ ብቻ መሆኑን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ነው:: አሊያ ያለው መንግስት አፋኝነትን ሆን ብሎ የሚመርጥ ግን ደግሞ ይህንን የማስፈፀም ዝግጁነት ወይም አቅም የሌለው ነው የሚል እንደምታን ያስከትላል:: በሌላ አባባል አፋኝነት ምርጫው ከሆነ የሚመጥን ዝግጁነት ሊኖረው፣ ምርጫው ሆኖ የማስፈፀም አቅም የለውም ከተባለ ደግሞ ከነሚስተር ዶናልድ ፔይን ድጋፍ ውጪ ተገርስሶ ግብዓቱ ከተፈፀመ የቆየ መሆን አለበት::/ነበረበት:: ይህ እኩል እውነት ሊሆን አይችልም::

አሸናፊ የነበረው ቅንጅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን አለመረከብ እና መንግስት «ለከተማዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ማቋቋሙ» በተመሳሳይ መታየት ያለበት ነው:: ይኸውም በተራ ቁጥር 7 እንደተጠቀሰው ይህ የሆነው ከምርጫው አንድ ዓመት በኋላ በ1998ዓ.ም ግንቦት ወር መሆኑ፣ እንዲሁም እስከዚያ ድረስ አሸናፊው ፓርቲ የከተማዋን አስተዳደር እንዲረከብ (በወቅቱ በህዳር ወር በቁጥጥር ስር ከዋሉት መሪዎች ውጪ ያሉትን ጨምሮ) የተደረገው መጠበቅ ውጤታማ ሳይሆን በመቅረቱ የተወሰደ እርምጃ የመሆኑን ተያያዥ እውነት የዘነጋ ነው:: ከሁሉም በላይ በዚሁ በተራ ቁጥር 7 አርቃቂዎቹ የጠቀሱትን *«...ካሸነፉት 170 መቀመጫዎች 150 ያህል የሚሆነውን ይዘው ተቃዋሚዎች ፓርላማ»* የመግባታቸውን እውነትም የሚቃረንና የሚገፋ ነው:: በተጨማሪም የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ ሂደት እና ልማት በአጠቃላይ በመመዘን ጥያቄ ውስጥ ከትተው አርቃቂዎቹ የሰጡትን ብይን ለማሳለፍ መነሻ የሆናቸው ቁጥራቸው ከሃያ የማይበልጥ እምቢተኛ የተቃዋሚ መሪዎች በሀገሪቱ ህግ መሰረት ተከስሰው ለእስር መብቃታቸውን ብቻ እንደሆነ ያሳያል::

በክፍል አንድ ፅሑፌ ከጠቀስኩት በታሳቢ ግቦችና በአፈፃፀም ስልት ደረጃ የሚስተዋል ከይዘት ትርጓሜ የመነጨ የተገቢነት መሰረት ጉድለት፣ ከረቂቁ እያጣቀስን ከፍ ሲል በጠቀስነው የአርቃቂዎቹ የግንዛቤና የፍላጎት መነሻ ደረጃም የሚያጋጥም ነው:: በዚህ የተነሳም ኤች አር 2003 በኮንግሬስ ፊት ቀርቦ፣ አጠያያቂ በሆነው በጥቅል የእሺታ ወይም እምቢታ የቃል ድምፅ አሰጣጥ (ቮይስ ቮቲንግ) ስነ ስርዓት ሽፋን ለመፅደቅ ከፈጀበት ግዜ ሲነፃፀር እጅግ በፈጠነ መልኩ ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ ወደሚለው የውድቀት ቁልቁለት ሊሽጋገር በቅቷል:: ንጉሡም አጃቢዎቻቸውም እርቃናቸውን ቆመዋል:: በቀጣዩ ክፍል ሶስት የደጋፊዎችን ዋነኛ የመከራከሪያ ጭብጦች በማንሳት ይህንኑ ለማሳየት እሞክራለሁ::